# የጉዞ መረጃዎችን መሰብሰብና እቅድ ማወጣት

አሽከርካሪዎች መረጃ ለመሰብሰብና ለማስተላለፍ  የማስታወሻ ደብተር፤ ሬዲዮና ሞባይል ፡ቪዲዮ ካሜራና ፎቶ ካሜራ የመሳሰሉትን መጠቀም ይችላሉ፡፡

## 1. የጉዞ መዳረሻ

አንድ አሽከርካሪ ጉዞውን ከመጀመሩ በፊት የጉዞውን ርቀትና መዳረሻውን ማወቁ የሚከተሉተን ጠቀሜታ ይሰጠዋል፡፡

- የጉዞ እቅድ በትክክል ለማዘጋጀት
- ተሽከርካሪውን ለጉዞ ለማዘጋጀት
- የነዳጅ መጠን ለማወቅ
- የጉዞ ግዜን በአግባቡ ለመተቀም
- በስነ ልቦና ለመዘጋጀት

# 2. የመንገድ ላይ መረጃዎች

የመንገድ ካርታዎችን ማንበብእጅግ የሚረዳ ሲሆን በጉዞ ወቅትከግምት ውስጥ መግባት ከሚገባቸው የአገልግሎት አይነቶች መካከል፡፡

- የነዳጅ ማደያዎች
- ሆቴሎች
- የስልክ አገልግሎት መስጫ
- የፖሊስ ስልክ አድራሻ
- ባንክና ኢንሹራንስ
- የአውቶቢስ ማቆሚያ

# 3. የመንገድ ሁኔታዎች መረጃ

**የመንገድ ደረጃ/ዓይነት/**

- አስፓልት
- ኮሮኮነረች
- አንሸራታች

**የመንገዱ መልከዓ ምድራዊና የመስመሩ ሁኔታ**

- ወጣ ገባ
- ከርቭ
- ቁልቁለት
- ዳገት

**አከባቢያዊ የአየር ሁኔታ**

- ነፋሻማ
- ጸሀያማ
- ደመናማ
- ዝናባማ

# የጉዞ ሰነዶች እና መረጃዎች

**የግል መረጃዎች**

- መንጃ ፈቃድ
- የመታወቂያ ካርድ
- ፓስፖርር

**ከስራ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰነዶች**

- ለጭነት የተሰጠ የይለፍ/መውጫ/
- ፍተሻ የማያስፈልግ መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ
- የጭነት አይነት መግለጫ
- የኢንሹራስ ምስክር ወረቀት

# የማህበረሰቡ ቋንቋ፡ባህልና ሀይማኖት

- አሽከርካሪዎች በጉዞ መስመር ላይ የሚገኙ ማህበረሰብ ቋንቋ፡ ባህል፡ ሀይማኖት፤ እመነትና እሴትጉዞ ከመጀመራቸው በፊት ለመረዳት መሞከርና በጉዞ ላይም ልብ ብለው ማስታወሻ መውሰድ አለባቸው፡፡

# የጉዞ መስመር አመራረጥ

- አሽከርካሪዊች ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት የተሸለ የመንገድ አይነትና ሁኔታ በመምረጥ ለአደጋ ተጋላጭነትን በመቀነስ የሚገባቸው ሲሆን መንገዱ በተቻለ መጠን ምቹና  የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚገኙበት መሆን ይኖርበታል፡፡አሽከርካሪዎች የጉዞ መስመር በሚመርጡበት ግዜ የመንገዱን ስፋት፤ የመንገዱን አይነትና የድልድዮች የመሸከም አቅም መረጃ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

# ምቹ መንገዶች መምረጫ መስፈርቶች

አንድ ጉዞ መስመሩ ምቹ የሚያደርገው ፡-

- ህጋዊና ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት መጀመሩ
- አደጋዎች በተደጋጋሚ የማያስተናግድ መሆኑ
- የተጨናነቀ የትራፊክ እንቅስቃሴ አለመኖሩ
- ብቃትና ደህንነት ከመንገድ ጥራትና ብቃት አንጻር መቃኘት